NMA ብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ
NATIONAL METEOROLOGY AGENCY

# የክረምት ወቅት አጋማሽ የአየር ጠባይ ትንበያ መጽሔት

## ከጁን -ጁላይ 2020 የአየር ጠባይ ግምገማ እና ከኦገስት-ስፕቴምበር 2020 የአየር ጠባይ ትንበያና ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2020
አዲስ አበባ

***ርዕስ*** ***ገፅ***


እ.ኤ.አ 2020 የክረምት አጋማሽ (ከጁን እስከ ጁላይ) የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ ወራት የሚኖረው አዝማሚያ ........ 1

እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2019 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ........ 2

ካርታ1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2020 ድረስ የነበረው ........ 3
የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ 3
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2020 ድረስ ዝናብ ........ 4
የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ........ 4
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/20 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ........ 5
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ 5

እ. ኤ. አ ከጁን እስከ ጁላይ 2020 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረዉ ተፅዕኖ ........ 6

ካርታ 4 ሀ እ.ኤ.አ ጁን 2020 የእርጥበት ደረጃ ጠቋሚ ካርታ 4 ለ እ.ኤ.አ ጁላይ 2020 የእርጥበት ደረጃ ጠቋሚ ........ 7

እ.ኤ.አ ከጁን እስከ ጁላይ 2020 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ 8

ካርታ 5ሀ፡ በጁን ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን ካርታ 5ለ፡ በጁላይ ወር በተፋሰሶ ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን ........ 8 ........ 8

እ.ኤ.አ ከጁን እስከ ጁላይ 2020 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ 9

ካርታ 6ሀ፡ በጁን ወር ለወባ መፈጠር አመቺ የሆኑ ቦታዎች ካርታ 6ለ፡ በጁላይ ወር ለወባ መፈጠር አመቺ የሆኑ ቦታዎች ........ 9 ........ 9

እ.ኤ.አ ከኦገሰት እስከ ሴፕቴምበር 2020 ሊኖር የሚችለው የአየር ጠባይ አዝማሚያ ........ 10

እ. ኤ. አ ከኦገሰት እስከ ሴፕቴምበር 2020 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 11

እ.ኤ.አ ከኦገሰት እስከ ሴፕቴምበር 2020 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 12

እ.ኤ.አ ከኦገስት እስከ ሴፕቴምበር 2020 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ 12

# እ.ኤ.አ 2020 የክረምት አጋማሽ (ከጁን እስከ ጁላይ) የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማና በቀሪዎቹ ወራት የሚኖረው አዝማሚያ

## 1. መግቢያ

የዘንድሮው የክረምት ወቅት እንደተጠበቀው መደበኛውን ፈር በተከተለ ሁኔታ በምእራባዊው የሀገሪቱ አካባቢ ላይ የጀመረ ሲሆን፤ ቀደም ብሎም ለወቅቱ የተሰጠው ትንበያ በአብዛኛው የሀገሪቱ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ በመስፋፋትና በመጠናከር የተሻለ ገጽታ ሊኖረው እንደሚችል ከመገለጹም በላይ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊያጋጥም እንደሚችል መጠቆሙ ይታወሳል:: ከላይ ለተጠቀሰው ትንበያ በዋናነት ታሳቢ የተደረጉት የባህር ወለል ሙቀት (Sea sea surface temperature) የጥንካሬ መጠንና ሥርጭት ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር ከሚያሳየው ልዩነት (anomaly) እንዲሁም ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚከሰቱትን የከባቢ አየር ክስተቶች (Atmospheric conditions) ግምት ውስጥ በማስገባት ነበር::

በመሆኑም ባለፉት ሁለት ወራት የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ የዉሃ አካል ከመደበኛዉ ጋር የተቀራረበ (ENSO-Neutral) የተስተዋለበት ሲሆን፤ የህንድ ውቅያኖስ ሰሜናዊዉ ክፍሉ የውሃ አካል በ(Near-neutral IOD) ክስተት ስር መሆኑ ከደቡብ ንፍቀ ክበብ የምድር ወገብን አቋርጦ ወደ ሀገራችን የሚገባው እርጥበት አዘል አየር መጠናከር አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንደሚኖረዉ ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ባለፉት የጁንና የጁላይ የክረምት ወራት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የተስተዋለ ሲሆን፤ በአንዳንድ ቦታዎችም ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ በ24 ሰዓት እንደተመዘገበ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በተመሳሳይ በቀሪዎቹ ሁለት ወራትም (ኦገስትና ሴፕቴምበር) በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ዝናቡ ቀጣይነት እንደሚኖረው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡


## እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2019 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በጁንና በጁላይ ወራት የነበረው የዝናብ መጠን ሲገመገም በምዕራብ አማራ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በምዕራብና መካከለኛዉ ኦሮሚያ እንዲሁም በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ላይ ከ400-1200 ሚሜ የሚደርስ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ በትግራይ፣ በአፋር፣ በምስራቅ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ደጋማ ስፍራዎች፣ በጋምቤላ ከ25-400 ሚሜ የሚደርስ ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን የደቡብ ኦሮሚያ ቆላማ ቦታዎች ላይ ለተወሰኑ ቀናት መጠነኛ ዝናብ ተመዝገቧል (ካርታ 1)።


በዝናብ ቀናት ስርጭት ረገድ ባለፉት ሁለት ወራት ምዕራብና መካከለኛው ትግራይ፣ ምዕራብ አማራ፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ ምዕራብና መካከለኛው ኦሮሚያ፣ የጋምቤላ ዞን 1፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሰሜናዊ አጋማሽ እንዲሁም አዲስ አበባን ጨምሮ ከ30-55 ቀናት ዝናብ ያገኙ ሲሆን፤ ምሥራቅ ትግራይና አማራ፣ አፋር፣ ምሥራቅ ኦሮሚያ፣ ሰሜን ሶማሌ፣ ድሬዳዋና ሐረሪ እንዲሁም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ደቡባዊ ክፍል ከ5-30 ቀናት ያህል የክረምት ዝናብን አግኝተዋል (ካርታ 2)።

ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2020 የዘነበው ዝናብ ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር አብዛኛዎቹ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች መደበኛውን ዝናብ ያገኙ ሲሆን፤ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ሸዋ፣ ደቡብ ኦሞ፣ አርሲና ባሌ፣ ጉጂና ቦረና፣ ምሥራቅና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምዕራብ ጎጃም፣ መካከለኛዉ ትግራይ እና የሲቲ ዞን በከፊል ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 3) ።


ካርታ1 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2020 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/2020 ድረስ ዝናብ
የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3  ኢ.ኤ.አ ከጁን 1 እስከ ጁላይ 31/20 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



## እ. ኤ. አ ከጁን እስከ ጁላይ 2020 የነበረው የአየር ጠባይ በእርሻ ሥራ ላይ ያሳደረዉ ተፅዕኖ


ባለፉት ሁለት የክርምት ወራት የእርጥበቱ ሁኔታ በአብዘሃኛዉ ክረምት ተጠቃሚ የአገሪቱ ክፍሎች ለመኸር የግብርና ስራ እንቅስቃሴ ጥሩ አስተዋፅኦ ነበረዉ፡፡

ባለፈው የጁን ወር ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች መደበኛውን ፈር ተከትለው የጀመሩ ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ የዝናቡ ስርጭትና መጠን አብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያደረሰ ነበር፡፡ ይህም የተገኘው ዝናብ የአፈርን እርጥበት ያሻሻለ ሲሆን ከጁን ጀምሮ የዘር ጊዜና የማሳ ዝግጅት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች በወቅቱ ለመዝራት አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል፤ አስቀድምው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች የውኃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር በተለይም ከኤፕሪል ጀምሮ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ የጎላ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአርብቶ አደርና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው አነስተኛ እርጥበት ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ እንዲሁም ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በሚገኙ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት እና በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ለወንዝ መሙላትና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ ለጎርፍ መከሰት ምክንያት ሆኖ ነበር፡፡እንድሁም በብልግ አብቃይ አከባቢዎች ላይ የነበረዉ ደረቅ ሁኔታ የደረሱ የበልግ ሰብሎችን ለመሰብሰብ ጥሩ አስተዋጽኦ ነበረዉ፡፡


ባለፈው የጁላይ ወር ለክረምት ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታ የሚፈጥሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች የነበሩ በመሆኑ በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች በተለይም ከሁለተኛዉ አስር ቀናት ጀምሮ ከቦታ ቦታ በመጠን ይለያይ እንጂ በስርጭት ረገድ ብዙ ቦታዎችን ያደረሰ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ ይህም የተገኘው ዝናብ የአፈርን እርጥበት ከማሻሻልም አልፎ ከጁላይ ጀምሮ ለሚዘሩ የተለያዩ የመካከለኛ ጊዜ ሰብሎች የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና በታቀደዉ መሰረት የግብርና እንቅስቃሴን ለማከናወን አመቺ ሁኔታ የነበረው ሲሆን፤ አስቀድምው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግ ሰብሎች የውኃ ፍላጎታቸውን ከሚሟላት አንፃር የጎላ ሚና ከመኖሩም በላይ ከኤፕሪል ጀምሮ ቀደም ብለው ለተዘሩ እንደ በቆሎና ማሽላ ለመሳሰሉ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለተለያዩ ቋሚ ተክሎች በተሟላ ሁኔታ እንዲያድጉ የጎላ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአርብቶ አደርና በከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ከማበርከቱም በላይ ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምንጮችን ከማጎልበት አንፃር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በአንፃሩ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ እንዲሁም ባሳለፍናቸው ቀናት በተከታታይ ዝናብ በማግኘት ላይ በነበሩ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት እና በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ለወንዝ መሙላትና ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የጎርፍ መከሰት የነበረ ሲሆን በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከንፋስ ጋር የተቀላቀለ ከባድ ዝናብ ለመጥቀስም ያህል በባህርዳር፣ በቴፒ በአብዛኛው ምዕራብና ሰሜን ምዕራብ የተከሰተው ጎርፍ በተለያዩ ሰብሎች እና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳስከተለ የደረሰን መረጃ ያመለክታል:: በተጨማሪም በመደበኛ ባህሪያቸው በእርጥበት መብዛት በሚታወቁ ሰፍራዎች ላይ ተከታታይነት የነበረው እርጥበታማ  ሁኔታ በሰብል ማሳዎች ላይ የውሃ መተኛት ያስከተለ ሲሆን ይህም ሁኔታ እየተከናወነ በሚገኘው የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ላይ መጠነኛ የሆነ አሉታዊ ጎን ነበረው፡፡

በአጠቃላይ እ.ኤ.አ 2020 ባለፉት ሁለት ወራት በእርሻ ስራ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው የአየር ሁኔታ  ለአብዛኛው ለመኸር አብቃይና ተጠቃሚ አከባቢዎች አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ ይህም የተገኘው እርጥበት ለዘር ጊዜ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ፣ በቡቃያ እና በእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ቋሚ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት፤ እንዲሁም በአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢዎች ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ ሆኖም በተወሰኑ የአገሪቱ አካባቢዎች በተለይም በጋቲራ፤ ጅንካ፤ ባህርዳር፤ ቴፒ፤ አዊ፤ ሰሜን ጎንደር፤ ምስራቅ ጎጃምና ሰሜን ጎንደር ላይ ከጣለው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በእርጥበት መብዛትና በጎርፍ መከሰት  ምክንያት በተዎሰነ መልኩ በሰብሎችና በንብርት ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡እንድሁም በአፋር ክልል የአዋሽ ወንዝ በመሙላት ለሰዎች መፈናቀልና በንብረት ላይ  ጉዳት አስከትሏል (ካርታ 4 ሀ እና ለ)፡፡





ካርታ 4 ሀ እ.ኤ.አ ጁን 2020 የእርጥበት ደረጃ ጠቋሚ




ካርታ 4 ለ እ.ኤ.አ ጁላይ 2020 የእርጥበት ደረጃ ጠቋሚ

## እ.ኤ.አ ከጁን እስከ ጁላይ 2020 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ሁለት የክረምት ወራት በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የተስተዋለው በሰኔ ወር በአብዛኛው ተከዜ፣ አባይ፣ ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ የላይኛው አዋሽ፣ በጥቂት የላይኛው ዋቢሸበሌ፣ አፋር ድናክል እንዲሁም የላይኛውና መካከለኛው ገናሌዳዋ ከፍተኛ ቦታዎች የነበረው የተሻለ እርጥበት ለግድቦችና ለወንዞች ፍሰት መጨመር የጎላ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ በጁላይ ወርም በአብዛኛው ተከዜ፣ አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ የላይኛውና መካከለኛው አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቢሸበሌ እና የላይኛው ገናሌዳዋ የተሻለ እርጥበት መጠን ተስተውሏል፡፡ በዚህ መሰረት በአብዛኛው ተከዜ፣ አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ የላይኛውና መካከለኛው ኦሞጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ እና አዋሽ ለግድቦችና ለወንዞች ፍሰት መሻሻል በተመሳሳይ መልኩ ጠቀሜታው የጎላ ነበር፡፡ በተጨማሪም በጥቂት የታችኛው ባሮአኮቦ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ የመካከለኛው አፋርደናክል፣ ዋቢ ሸበሌ እና ገናሌዳዋ ኪስ ቦታዎች መጠነኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡በሌላ በኩል በአብዛኛው ኦጋዴን፣ የታችኛው አፋርደናክል፣ ገናሌ ዳዋ እና ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም የታችኛው አዋሽ ተፋሰሶች ደረቅና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ነበራቸው (ካርታ 5ሀ እና 5ለ)፡፡





ካርታ 5ሀ፡ በጁን ወር በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን




ካርታ 5ለ፡ በጁላይ ወር በተፋሰሶ ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን

## እ.ኤ.አ ከጁን እስከ ጁላይ 2020 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ ባሳለፍነው በጁን 2020 ለወባ መፈጠር ምቹ የዝናብ፣ ሙቀትና ምዝን የአየር ርጥበት የአየር ሁኔታ የነበረባቸው ቦታዎች በአብዛኛው ምዕራብ አማራ ክልል፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ምዕራብና መካከለኛው ኦሮሚያ፣ ደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ጋምቤላ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ለወባ መፈጠር ምቹ የአየር ሁኔታ እንዳልነበር ያሳያል። እ.ኤ.አ ባሳለፍነው በጁላይ 2020 ለወባ መፈጠር ምቹ የዝናብ፣ ሙቀትና ምዝን የአየር ርጥበት የአየር ሁኔታ በትግራይ፣ በአብዛኛው አማራ ክልል፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ምዕራብ ምስራቅና መካከለኛው ኦሮሚያ፣ ደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ጋምቤላ በመሳሰሉት ቦታዎች ላይ ተስፋፍቶ ተስተውሏል (ካርታ 6 ሀ እና ለ)፡፡




ካርታ 6ሀ፡ በጁን ወር ለወባ መፈጠር አመቺ የሆኑ ቦታዎች




ካርታ 6ለ፡ በጁላይ ወር ለወባ መፈጠር አመቺ የሆኑ ቦታዎች

***<u>መግለጫ፡-</u>*** **በቢጫ ባክግራዉንድ ቀይ መስመር ካሬ ያለባቸው ቦታወች ለወባ መፈጠር አመቺ የአየር ሁኔታ ያለባቸው ቦታወች ናቸው**

በመደበኛ ሁኔታ የኦገስት ወር የክረምት ዝናብ በመጠንም ሆነ በሥርጭት በክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ከፍተኛ ደረጃ የሚደርስበት ጊዜ ነው። በተጨማሪም በኦገስት ወር በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በፀሐይ ሀይል ታግዘዉ ከሚፈጠሩ የደመና ክምችቶች በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ አልፎ አልፎ ይከሰታል።

በሚቀጥሉት ሁለት የክረምት ወራት (ከኦገሰት እስከ ሴፕቴምበር) በአሁኑ ጊዜ የትሮፒካል ፓስፊክ ውቅያኖስ ምስራቃዊውና የመካከለኛው ክፍል የባህር ወለል የሙቀት መጠን (Near-neutral ENSO) ላይ የሚገኝ ሲሆን በቀሪዎቹ የክረምት ወራትም ከመደበኛው ጋር በተቀራረበ ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖረዉና በሂደትም በወቅቱ መጨረሻ ላይ ግን ከመደበኛው በታች የፓስፊክ የባህር ወለል ሙቀት(La Niña) የመሆን እድሉ ከ50-55% እንደሚሆንና በበጋ ወቅትም ቀጣይነት እንደሚኖረዉ መረጃዎች ያመላክታሉ። ከዚህም ሌላ የሰሜናዊ ህንድ ውቅያኖስ የባህር ወለል ሙቀት በ(Near-neutral IOD) ስር እንደሚገኝና በቀጣይ ግን (weak Negative-IOD) የመሆን እድል ሊኖር እንደሚችል ከተለያዩ አለም አቀፍ የትንበያ ማዕከላት የተገኙ የዳይናሚካልና የስታትስቲካል መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ይህም ሁኔታ ከደቡባዊው የህንድ እና የአትላንቲክ ውቅያኖሶች ወደ ሀገሪቱ ሊገባ የሚችለው እርጥበት በቀሪዉ የክረምት ወራትም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ግንዛቤ ተወስዷል።

<u>በዚሁ መሰረት በቀጣዮቹ ሁለት የክረምት ወራት </u>(ከኦገሰት እስከ ሴፕቴምበር) <u>የሰሜንምእራብና የምእራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠን እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን! አብዛኛዉ የደቡብምእራብ፣ የመካከለኛዉ፣ የምስራቅና የደቡብ ደጋማ እንድሁም የሰሜንምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከመደበኛው በላይ የሆነ ዝናብ የማግኘት እድል ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል ይጠበቃል። በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚፈጠሩ ነጎድጓድ አዘልና በረዶ የቀላቀለ ከባድ ዝናብ ጋር በተያያዘ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የወንዞች ከመጠን በላይ መሙላት እንዲሁም ቅጽበታዊ ጎርፍ በረባዳማ ቦታዎች እና ጎርፍ በሚያጠቃቸው አካባቢዎች ላይ የመከሰት እድል ቀጣይነት ሊኖረዉ ይችላል። ስለሆነም ከጎርፍና ከወንዞች ዉሃ ሙላት ጋር ተያይዞ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑት ዝቅተኛ ስፍራዎችና በወንዞች ተፋሰስ አካባቢ የሚኖሩ የህብረተሰቡ ክፍሎችና የሚመለከታቸዉ ከወዲሁ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ እናሳስባለን።</u>

<u>በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ አወጣጥ በተመለከተ መስከረም የመጀመሪያዎቹ ቀናት አካባቢ ከሴሜንምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ዝናቡ መዳከም የሚጀምር ሲሆን ቀስ በቀስ ወደ ደቡባዊ የሀገሪቱ አካባቢዎች በማፈግፈግ በኖቨምበር መጀመሪያ ሳምንት ላይ ከሁሉም አካባቢዎች ላይ ዝናቡ ያቆማል። የዘንድሮ የክረምት ዝናብ አወጣጥ በተመለከተ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ የክረምት ዝናብ</u>

ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ መደበኛውን ፈር በተከተለ ሁኔታ የማቆም አዝማሚያ ሊኖረው እንደሚችል ይጠበቃል፡፡

በሌላ በኩል በመጪዉ የበጋ ወቅት የሚጠበቀዉ (weak Negative-IOD እና La Niña) የወቅቱ ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የደቡብና የደቡብምስራቅ የሀገሪቱ ቆላማ አካባቢዎች ላይ የዝናብ ማነስ እድል ሊያስከትል እንደሚችል ከወዲሁ ቅድመ-ጥቆማ መስጠት ይቻላል፡፡

## እ. ኤ. አ ከኦገሰት እስከ ሴፕቴምበር 2020 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

ለመጪዎቹ ሁለት ወራት (ኦገስት እና ሴፕቴምበር) በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በመጠንም ሆነ በስርጭት በቂ የእርጥበት መጠን ከላይ በተጠቀሱት በተለይም በደቡብ ምእራብ፤ በመካከለኛዉ፤ በደቡብ ከፍተኛ ቦታዎች፤ በሰሜን ምስራቅ፤ በምእራብና በሰሜን ምእራብ የመኸር አብቃይና ተጠቃሚ አካባቢዎች ለእርሻ ስራ እንቅስቃሴ አመቺ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ ይህም ሁኔታ በመኸር ወቅት ለሚመረቱ ለመካከለኛና ለረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገት፣ ለቋሚ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት፣ ዘግይተዉ ለተዘሩ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች አካባቢ ለሚገኙ ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ከመደበኛ በላይ ዝናብ በሚጠበቅባቸዉ አካባቢዎች በመጪው ኦገስት ካለፈው ጁላይ ወር በተሻለ ሁኔታ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ እርጥበቱ ከመጠን በላይ ሊሆን ስለሚችል በዚህም ምክንያት ውሃ ማሳ ላይ እንዳይተኛ ቦይ በማውጣት፣ የማጠንፈፍና የመከላከል ስራ በመስራት እንዲሁም አረምን በወቅቱ በማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን በወቅቱ ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ በመደገፍ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በመጨረሻም በትንበያው መሰረት ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸውና በውኃ መብዛት በሚጠቁ ቦታዎች አርሶ አደሩ እና የሚመለከታቸው አካላት በጋራ በመሆን በሰብሎች፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በተጨማሪም የሚጠበቀው ቀጣይነት ያለው የእርጥበት ሁኔታ በክረምት ወቅት መጨረሻ በአፈር ውስጥ በተከማቸው እርጥበት በመታገዝ በደጋማው አካባቢዎች ላይ ለሚዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ አልፎ አልፎ በደቡብ የተወሰኑ አካባቢዎች የሚገኘዉ እርጥበት በአካባቢው ለሚኖሩት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሣርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት ጥሩ አስተዋጽዖ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ በአጠቃላይ በተቀሩት የክረምት ሁለት ወራት(ኦገስት እና ሴፕቴምበር) እርጥበቱ በመጠንም ሆነ በስርጭት አብዛኛው የክረምት አብቃይና ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ከእርጥብ እስከ በጣም እርጥብ ሆኖ እንደሚቆይ የሚጠበቀ ሲሆን ለግብርናዉ እንቅስቃሴ አወንታዊ ሚና እንደሚኖረዉ ይጠበቃል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦገሰት እስከ ሴፕቴምበር 2020 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የክረምት የመጨረሻዎቹ ሁለት ወራት ውስጥ እርጥበታማ የአየር ሁኔታ በተለይም በሰሜንና በምእራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ከምሥራቃዊው አጋማሽ አንጻር የተሻለ ሆኖ ሊቀጥል እንደሚችልና በተለያዩ ቦታዎች ላይ አልፎ አልፎ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል እንደሚችል የትንበያ መረጃዎችን ያመለክታሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ ባሮአኮቦ፣ የኦሞጊቤ የላይኛውና የመካከለኛው አዋሽ፣ ስምጥሸለቆ፣ ዋቢሸበሌ፣ አፋር ደናክል እና የላይኛው ገናሌዳዋ ተፋሰሾች ላይ ከከፍተኛ እርጥበት እስከ እርጥበታማ ሁኔታ ሊያገኙ እንደሚችሉ የሚጠበቅ ሲሆን በአንዳንድ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ላይ የሚዘንበውን ከፍተኛ ዝናብ ተከትሎ ቅፅበታዊ ጎርፍ እና የመሬት መንሸራተት ሊከሰት ስለሚችል ክትትልና ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም የታችኛው አዋሽ፣ ኦሞጊቤ እና ስምጥሸለቆ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደሚኖራቸው የሚጠበቅ ሲሆን በሌላ በኩል በአብዛኛው ኦጋዴን፣ የታችኛዉ ዋቢሸበሌ እና ገናሌዳዋ ተፋሰሶች ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ ሆነው እንደሚቆዩ ይጠበቃል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኦገስት እስከ ሴፕቴምበር 2020 የነበረው የአየር ጠባይ በጤናው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪው በኦገስትና ሴፕቴምበር ለወባ መፈጠር ምቹ የአየር ሁኔታ ምዕራብ ትግራይ፣ ምዕራብና ምስራቅ አማራ፣ ምዕራብና ደቡብ አፋር፣ ምዕራብና ምስራቅ ኦሮሚያ፣ ደቡብ ሶማሌ፣ በአንዳንድ የሀረርጌ ዝቅተኛ ቦታዎች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ደቡብ ምዕራባዊ ክፍል፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ እና ጋምቤላ አካባቢዎች ይጠበቃል። በመሆኑም ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት የተሰጠውን ትንቢያ መሰረት በማድረግ ከፍተኛ የሆነ ክትትልና ጥንቃቄ እንዲደረግ እንመክራለን። በተጨማሪም በወንዞች ዙሪያ እንዲሁም ለጎረፍ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ ማህበረሰቦች በዉሃ ወለድ በሽታ የመጠቃት ዕድላቸው ከፍተኛ ሊሆን ስለሚችል የሚመለከታቸው አካላት እንዲሁም ማህበረሰቡ ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረጊ አለባቸው፡፡